# የጎንደር ጦርነት የአርበኞች ድል የፋሽስት ኢጣልያ የመጨረሻ ውድቀት

ወራሪው የፋሽስት ጣሊያን ጦር በጀግኖች አርበኞች ተጋድሎና በእንግሊዝ ረዳትነት ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ድል ሆኖ አዲስ አበባን ከለቀቀ በኋላ የተቀረው የጠላት ጦር የምስራቅ አፍሪካ የኢጣሊያ ጦር የበላይ አዛዥ በሆነው በዱክ ዳምስታ አመራር ስር ደሴ ላይ መሽጎ ሲጠባበቅ የቀረው ጦር እንዲሁ የምስራቅ አፍሪካ ምክትል ጦር አዛዥ በሆነው በጄኔራል ናዚ አመራር ጎንደር ላይ መሽጎ የሙሶሎኒን እርዳታ ይጠባበቅ ነበር፡፡

ይሁንና ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በድል አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ አርበኛው እንደቀደመው ከእንግሊዝ ጦር ጋር በመተባበር የጠላትን ጦር እየደመሰሰ አዲስ አበባ በድል እንደገባ ሁሉ አሁንም በየሃገሩ መሽጎ የተቀመጠውን የጠላት ጦር ከእንግሊዝ ጦር ጋር በመተባበር እንዲደመስስ በሰጡት ትእዛዝ መሠረት በተለይም በደሴ እና በጎንደር መሽጎ የተቀመጠውን የዱክ ዳምስታንና የጀነራል ናዚን ጦር እንዲደመስሱ ከግርማዊነታቸው የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ተቀብለው ደጃዝማች ኃብተሥላሴ በላይነህ አርበኞቻቸውን ይዘው ወደ ሰሜን ዘመቱ፡፡



ደጃዝማች ኃብተሥላሴ በላይነህ (አባ ጉራች)

በመጀመሪያም እነ ደጃዝማች ኪዳነወልድን ፊታውራሪ ከበደ ካሣን እንዲሁም ሌሎች የጦር አለቆችን በማስከተል የዱክ ዳምስታን ጦር ለመደምሰስ ከሸዋ ተነስተው ወደ ደሴ ጉዟቸውን ቀጠሉ፡፡

ዱክ ዳምስታ የኢጣሊያው ንጉሥ የቪክቶር አማኑኤል ሶስተኛ የወንድም ልጅ ሲሆን ሙሶሎኒ ጄኔራል ግራዚያኒ በቅፅል ስሙ (የአዲስ አበባው አራጅ ወይም Butcher of

Addis Abeba) በሕዝቡ ላይ የሚፈፅመው ግፍ እየበዛ ስለሄደና እያመፀ ወደ አርበኝነት የሚገባው ህዝብ እየጨመረ መሄዱ ስላሳሰበው ይህንኑ በዲፕሎማሲ መንገድ እንዲያሻሽል በማለት በግራዚያኒ ፋንታ ሾሞት ነበር ::

ይሁንና ሙሶሎኒ ከሒትለር ጋር በማበሩ የተነሳ የተባበሩት የጦር ቃል ኪዳን ሃገሮች በከፈቱበት ጥቃትና በጀግኖች አርበኞቻችን ተጋድሎ አዲስ አበባ ስትያዝ ዱክ ዳዎስታ ወደ ደሴ በመሸሽ አምባላጌ ላይ መሽጎ በከፍተኛ የስንቅ እና ትጥቅ ችግር በተለይም በነዳጅ እጥረት እየተሰቃየ የሙሶሎኒን እርዳታ ይጠባበቅ ነበር።

ከዚህ በኋላ በግንቦት ወር ፲፱፻፴፫ ቁጥራቸው ወደ ሃያ ሺህ በሚገመቱት አርበኞችና ወደ ዘጠኝ ሺህ በሚገመቱት የእንግሊዝ ወታደሮች አምባላጌ ላይ ተከቦ ሲከላከል ከቆየ በኋላ የውሃ አቅርቦቱ ስለተያዘበት ግንቦት ፲ ቀን ፲፱፻፴፫ እጁን ሰጠ።

ከዚያም በኋላ የጦር እስረኛ ሆኖ ወደ ኬንያ ከተላከ በኋላ በጦር ካምፕ ውስጥ እያለ በያዘው የሳንባና የወባ በሽታ ሲሰቃይ ቆይቶ የካቲት ፳፫ ቀን ፲፱፻፴፬ ዓ.ም በሞት ተለየ።

በዚህም ድል ከፍተኛ ደስታ የተሰማቸው አርበኞች ውጊያቸውን በመቀጠል ጎንደር ላይ መሽጎ የሚጠብቀውን የጀነራል ናዚን ጦር ለመደምሰስ ጉዟቸውን ቀጠሉ።


በመንገዳቸውም የጠላትን ምሽጎች እየደመሰሱ ጎንደር ደርሰው ጎንደር ከዘመተው በጄኔራል ቻርልስ ፎክስ ከሚመራው የእንግሊዝ ጦር ጋር ከተገናኙ በኋላ ደጃዝማች ኃብተ ሥላሴ ጥቃት በሚሰነዝሩበት ሁኔታ ላይ ከጄኔራል ቻርልስ ፎክሰ እና ከጄኔራል ዊልያም ፕላት ጋር ከተነጋገሩ በኋላ ዝግጅታቸውን ቀጠሉ ::




በደጃዝማች ኃብተሥላሴ የሚመሩት አርበኞች ጎንደር ላይ

ጄኔራል ናዚ ጎንደር ላይ አርባ ሺህ የሚገመተውን ሰራዊቱን ሰብስቦ የጎንደርን ዙርያ በከፍተኛ ፀረ ተሽከርካሪና እና ፀረ ሰው ፈንጂ በመድፍና በመትረየስ አጥሮ እንዲሁም በከፍተኛ ሜካናይዝድ ጦር ምሽጉን አጠናክሮ ሂትለር የተባበሩትን የጦር ቃል ኪዳን አባል ሃገራትን እያሸነፈ እንደሆነና በቅርቡም ለነርሱ እርዳታ እንደሚደርሳቸው የሓሰት ፕሮፕጋንዳ ለወታደሮቹ በመንዛት ጠንክረው እንዲዋጉ ያበረታታ ነበር ሙሶሎኒም የዱክ ዳዎስታን መማረክ እንደሰማ የምስራቅ አፍሪካ የኢጣሊያ ጦር የበላይ አዛዥ አድርጎ ሾመው፡፡

ከዚህ በኋላ በእንግሊዝ የጦር አዛዦች መሪነት ህዳር ፳ቀን ፲፱፻፴፬ ዓ.ም ወደ ጎንደር ከተማ የሚወስደውን ቁልቋል በር የተባለውን የጠላት ምሽግ ለማስለቀቅ የእንግሊዝ ወታደሮችና አርበኞች በመተባበር ጥቃት ሰነዘሩ ይሁንና ጥቃቱ በጥንቃቄ የተጠና ባለመሆኑ የእንግሊዝ ወታደሮችና አርበኞች በጠላት ዒላማ ውስጥ በመግባታቸው ከፍተኛ ዕልቂት ሆነ ብዙ ጀግኖች አርበኞችም ሰውነታቸው በፈንጅ እየተበጣጠሰ ወደቁ የእንግሊዝ የጦር አውሮፕላኖች ያደረጉትም የአየር ደብድባ ውጤት ባለማምጣቱ ጦሩ እንዲያፈገፍግ ተደርጎ ሌላ በቂ ዝግጅት ተደርጎ ከሳምንት በኋላ ጥቃት እንዲጀመር ተወሰነ፡፡



የፋሽስት ኢጣሊያ ታንክ ጎንደር ላይ መሽገው ሲጠባበቁ

በዚህ ጊዚያዊ ድል ከፍተኛ ደስታ የተሰማው ጄኔራል ናዚ እንደቀደመው ሁሉ በአውሮፕላን የፕሮፕጋንዳ ወረቀት በመበተን የማይደፈር መሆኑን ለማሳየት ጣረ፡፡

በዚህ ጥቃት አለመሳካትና የወንድሞቻቸው ዕልቂት የተበሳጩት ደጃዝማች ኃብተሥላሴ እና ሌሎችም የጦር አዛዦች ለሚቀጥለው ጥቃት የራሳቸውን ዕቅድ በማውጣት ሲዘጋጁ ቆዩ።

ጥቃቱም እንደተባለው ካንድ ሳምንት በኋላ ህዳር ፲፪ ቀን ፲፱፻፴፬ ዓ.ም ከጥዋቱ አንድ ሰዓት ተጀመረ ከሁለቱም ወገን ቀዝቅዝ ያለ የተኩስ ልውውጥ ሲካሄድ ከቆየ በኋላ ከቀኑ አምስት ሰዓት ሲሆን የእንግሊዝ መድፎች ምሽጉን በሃይል በመደብደባቸው በዚህ ማህል ፋታ ያገኙት አርበኞች በድንገት ወደ ምሽጉ ክልል በመግባት የታጠረውን ሽቦ እየቆረጡ በተጠመደው ፈንጂ ላይ አንዱ ባንዱ ላይ እየተረማመዱ የእጅ ቦንባቸውን በመንቀል በደረታቸው እየተሳቡ ወደ ጠላት ምሽግ በመግባት ያርበደብዱት ጀመር ከዚያም ፍርቃ በር የተባለውን ምሽግ ተቆጣጥረው ግስጋሴያቸውን በመቀጠል የቁልቋል በር ምሽግን ተቆጣጠሩት የምሽጉንም መሰበር ያየው የኢጣሊያኑ ጦር አዛዥ ኮሎኔል አጎሊኒ ነጭ ባንዲራ በማውለብለብ እጅ በመስጠቱ ጦርነቱ ወደ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ተጠናቀቀ።

ለዚሁም ድል ጄኔራል ፎክስ ለደጃዝማች ኃብተሥላሴ ያለውን አድናቆት ገልፆላቸዋል ይሁን እንጂ ጄኔራል ዊልያም ፕላት ወደ ሃገሩ ተመልሶ ለእንግሊዝ መንግስት ስለጦርነቱ ሪፖርቱን ባቀረበበት ወቅት ስለ ኢትዮጵውያኑ አርበኞች አንድም ያለው ነገር አልነበረም ይህንኑም ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ኢትዮጵያ እና የህይወቴ እርምጃ በተባለው መጽሃፋቸው «አርበኞቻችን ያገኙትን ድል ሁሉ እንግሊዞች የነሱ እንደሆነ አድርገው ይገልፁ ነበር»ብለው ፅፈውታል።

ከዚህ በኋላ ወደ ጎንደር ከተማ የሚወስደው በር ስለተከፈተ ሠራዊቱ ተጉዞ አዘዞ ሰፈረ ጄኔራል ናዚም ያለውን ሃይል ሁሉ አስተባብሮ እንደተለመደው አካባቢውን በፀረ ሰው እና በፀረ ተሽከርካሪ ፈንጅ አጥሮ የመጨረሻውን ፊልሚያ ለማድረግ ተዘጋጅቶ ይጠብቅ ነበር።

በመጨረሻም የጎንደር ከተማ በየአቅጣጫው ተከበበች፤

<u>በጠዳ በፈንጠር እና አዘዞ</u>

ደጃዝማች ኃብተሥላሴ በላይነህ፣ ደጃዝማች ኪዳኔ ወ/መድህን፣ ፊታውራሪ ከበደ ካሳ፣ ፊታውራሪ ተሰማ ዕርገጤ እና ሌሎችም

በእንግሊዝ ጦር በኩል ጄኔራል ቻርለስ ፎክስ፤ጄኔራል ዊሊያም ፕላት እና ሜጀር ዳግላስ

<u>በሰቀልት በልደታ</u>

ደጃዝማች በዛብህ በለው፣ ደጃዝማች ካሣ መሸሻ፣ ደጃዝማች ከበደ ወንድም አገኝ እና ሌሎችም

<u>በቁስቋም</u>

ደጃዝማች ብሬ ዘገየ፣ ደጃዝማች ጀንበሩ ብሩ፣ደጃዝማች ጫኔ የመረጡ እና ሌሎችም

በዚህ ሁኔታ የጎንደር ከተማ ከተከበበች በኋላ ህዳር አስራ ፲፰ ቀን ፲፱፻፴፬ ዓ.ም ከጠዋቱ አስራ ሁለት ሰዓት ጦርነቱ ተጀመረ የእንግሊዝ እና የጠላት መድፎች ሰማይና ምድሩን ያናውጡት ጀመር የእንግሊዝ የጦር አውሮፕላኖች ከዳባት በመነሳት የናዚን የጦር ሰፈር በቦንብ ይቀጠቅጡት ጀመር ።

በደጃዝማች ኃብተሥላሴ የሚመራው በደቡብ ጎንደር ሰፍሮ የነበረው አርበኛ ሌሊቱን ተጉዞ አድሮ ወደ ምሽጉ ተጠግቶ ስለነበር የጣሊያኑን የጄኔራል ማርቲንን ሠራዊት ሰብሮ ቀድሞ ጎንደር ገብቶ የጠላትን ጦር ያርበደብደው ጀመር በጄኔራል ፎክስ የሚታዘዘው የእንግሊዝ ሜካናይዝድ ጦር አዘዞን ግንባር ጥሶ ገባ በምስራቅ በኩል የነበሩት አርበኞችና የእንግሊዝ ወገን የሆኑት የኬንያ ወታደሮች ደፈጫ የነበረውን የጠላት ጦር በጥንካሬ ወግተው አስለቅቀው ወደ ጎንደር ለመግባት ሲሞክሩ በተጠመደ ፈንጂ ከባድ ጉዳት ደረሰባቸው፡፡

በዚህ ሁኔታ ውጊያው ቀጥሎ ውሎ በነጋታው የሌሊቱን መንጋት ሲጠባበቅ የነበረው አርበኛ በየቦታው የጣሊያንን ወታደር እያሳደደ ይገድል እና ይማርክ ጀመር ከዚህ በኂላ ጄኔራል ናዚ ከተደበቀበት ካዲ ኢጣሊያ ከሚባለው ቤት አስተርጓሚ ሆነው ሲያገለግሉት ከነበሩት ከፊታውራሪ አስፍሓ ወ/ሚካኤል ጋር በመሆን እጁን ሰጠ፡፡

ከዚህ በኂላ ሰራዊቱ እንዲረጋጋ የተማረኩና የተበተኑት የጠላት ወታደሮችም እንዲሰበሰቡ በተማረኩ የጠላት ወታድሮች ላይም አርበኞች ምንም ጉዳት እንዳያደርሱ የማረኳቸውን እንዲያስረክቡ የሚል ትዕዛዝ በመተላለፉ አርበኞች የማረኳቸውን የጠላት ወታደሮች እያመጡ ያስረክቡ ጀመር፡፡



ጎንደር የተማረከ የፋሽስት ኢጣሊያ ወታደሮች ጠመንጃ ክምር

በዚህ ጦርነት አራት ሺህ የጣሊያን ወታደሮች ሲገደሉ ስምንት ሺህ አራት መቶ የቆሰሉ ሲሆን ሃያ ሰባት ሺህ ተማርከዋል ጄኔራል ናዚም የጦር ወንጀለኛ ሆኖ በእስር ወደ ኬንያ ተላከ፡፡ ኢጣሊያ  ኢትዮጵያን ለዘመናት ቅኝ ግዛት አድርጋ ለመግዛት የነበራት ህልምም በዚህ ጦርነት በጀግኖች አርበኞቻችን ድል ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተደመደመ፡፡

ጦርነቱ ካለቀና ደጃዝማች ኃብተ ሥላሴ እና አርበኞቻቸው የያዙትን የጠላት ምሽግ እየተቆጣጠሩ ባለበት ሰዓት የእንግሊዝ ወታደሮች በማናለብኝነት አርበኞች የሚቆጣጠሩትን የፀጥታ ኬላ ለማለፍ ሲሞክሩ ካርበኞች ጋር ግጭት ፈጠሩ ይህንኑ ግጭት ደጃዝማች ኃብተ ሥላሴ እና ጄኔራል ፎክስ ካስቆሙ በኋላ ጄኔራል ፎክስ ደጃዝማች ኃብተሥላሴን ካርበኞቻቸው ጋር የያዙትን ምሽግ አስርክበው እንዲወጡ ጠየቃቸው እርሳቸውም ጥያቄውን እንደማይቀበሉት በመግለጻቸው ነገሩ እየተካረረ በመሄዱ ጄኔራል ፎክስ ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አርበኞቹ ምሽጉን አስረክበው እንዲወጡ እንዲያደርጉ በቴሌግራም በመጠየቁ ግርማዊነታቸውም  በእንግሊዞች በነበረባቸው ጫና አማራጭ ስላልነበራቸው ለደጃዝማች ኃብተሥላሴ ምሽጉን ለእንግሊዞች አስረክበው እንዲወጡ የሚል ታዕዛዝ አስተላለፉላቸው እርሳቸውም በስንት ተጋድሎ የያዙትን ምሽግ ከነጠቅላላ ንብረቱ አስረክበው ወጡ። እንግሊዞችም በምሽጉ ውስጥ የሚገኘውን በጊዜው ለኢትዮጵያ ሃገር መከላከያ ማደራጃ ሊጠቅም ይችል የነበረን በብዙ ሚሊዮን ብር የሚገመተውን የጦር መሳሪያ( ታንክ፣መድፍ፣ የጦር ተሽከርካሪ፣ ወዘተ) ወደ ኤርትራ አጓጓዙት ::



በግራ በኩል የሚታዩት ደጃዝማች ኃብተሥላሴ በላይነህ ጎንደር የጄኔራል ናዚን ጦር ድል አድርገው አዘዞ ከእንግሊዝ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ፩.ጄኔራል ፎክስ ፪.ጄኔራል ዊዝሮል ፫.ጄኔራል ጀምስ ፬.ሜጀር ዳግላስ ፭.ከወዳጃቸው ከካፒቴን ዴርክ ጋር የተነሱት ፎቶግራፍ ነው

ከዚህ በኋላ ጄኔራል ፎክስ ለማስተዛዘኛ  በሚመስል  መልኩ አራት መቶ ሽህ ብር ለደጃዝማች ኃብተሥላሴ ሰጥቷቸው ላርበኞቻቸው አከፋፍለውታል :: ከዚህ በኋላ ልዑል አልጋ ወራሽ ጎንደር መጥተው ስለነበር እርሳቸውን ተቀብለው ከርሳቸው ጋር ከቆዩ በኋላ ከነሠራዊታቸው ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው የካቲት ፲፮ ቀን ፲፱፻፴፬ ዓ/ም በታላቅ ሰልፍና ሥነ ሥርዓት ስድስት ዓመት ከተለዩዋቸው ንጉሠ ነገሥታችው ፊት ቀርበው ቆርጠጥ ቆርጠጥ ጎርደድ ጎርደድ አንዳንዴም በርከክ እያሉ ፤(በጊዜው ባንዲራችን የተባለው ጋዜጣ እንደፃፈው)

ኃብቴ ኃብተ ሥላሴ ⁞

ነብስ አሰናባች እንደ ሥላሴ⁞

የጠቅል አሽከር የንጉስ ተፈሪ ⁞

ለሃይማኖቱ ተከራካሪ ⁞

ጄኔራል ገዳይ ኒሻን ያሠረ ⁞

ማጆር ማራኪ የተከበረ ⁞

ያንተ አሽከር ያንተ ወታደር ⁞

በዘመተበት የማያሳፍር ⁞

ዘው ዘው ባይ ከጦሩ ማህል ⁞

ጄኔራል ናዚ አቤት አቤት ሲል ⁞

እያሉ ይህንንና ይህን የመሳሰለውን የፉከራ ቃል እየተናገሩ ከማይጨው ጀምረው እስካሁን ድረስ የሠሩትን ጀብዱ ሲቆጥሩ እንኳን ከዚህ በፊት ሥራ የሰራውን ቀርቶ ያልሰራውንም ዘራፍ ለገናው ለማለት ወኔውን ይቀሰቅሰው ነበር።



ክቡር ደጃዝማች ኃብተሥላሴ የናዚን ጦር ድል አድርገው በተመለሱ ጊዜ የካቲት ፲፮ ቀን ፲፱፻፴፬ ዓ.ም በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ፊት በታላቅ ጦር ሰልፍ ባለፉ ጊዜ የተነሱት ፎቶግራፍ ነው

ከዚህ በኋላ የማረኳቸውን ከባድና ቀላል መትረየሶች በማበርከት ያደረጓቸውን አግልግሎቶች ጠቅሰው ፤

«እኔ አገልጋይዎ እንኩዋን አይነዎን አይቼ ከፊትዎ ቀርቤ ድካሜንና ሙያዬን ተናገርኩ እንጂ እንግዲህ እኔ ይህንን እድል ካገኘሁ በኋላ እውነተኛ ባሪያዎ ነኝና ምንም አላሳስብም ብለው ቢናገሩ» ግርማዊ ጃንሆይ «ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ከመውደዱ የተነሣ እንግዲህ እናንተ ጌቶች ናችሁ እንጂ ባሮች አይደላችሁም እንዳላቸው ተወዳጅ ልጅ ነህ እንጂ ባሪያ አይደለህም ሥራህም በማንም አፍ የተመሰገነ ነው»ብለው ሞገሳዊ ቃል ሰጥተዋቸዋል።<ባንዲራችን ጋዜጣ ፩ኛ ዓመት፣ ቁጥር ፴፱ የካቲት ፲፰ ቀን ፲፱፻፴፩ ዓ.ም>




ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የካቲት ፲፯ ቀን ፲፱፻፴፩ የጀግኖች አርበኞቻቸውን ሰልፍና ፉከራ ሲመለከቱ

ደጃዝማች ኃብተሥላሴ በላይነህ፤

በመጋቢት ወር ፲፱፻፳፰ ዓ.ም ማይጨው ላይ በተደረገው ታላቁ ጦርነት ከክብር ዘበኞች ጋደኞቻቸው ጋር ሆነው ከፍ ባለ ጀግንነት ከጠላት ጋር በመዋጋት አገራቸውንና ንጉሠ ነገሥታቸውን አገልግለዋል። ከዚያም እንደተመለሱ በንጉሠ ነግሥታቸው መሪ ትዕዛዝ መሠረት የጦርነት ትግላቸውን በሰሜን ሸዋ በመቀጠል አምስት ዓመት ሙሉ በአርበኝነት የጦር መሪ በመሆን እጅግ ከፍ ባለ ጀግንነት ሌት ከቀን ያለ አንዳች አረፍት በየጦር ሜዳው

የጠላትን ኃይል ያንበረከኩ ታላቅ ጀግና ነበሩ የገደሏቸውንም የጠላት መኮንኖች ለመጥቀስ ያህል፣

፩. በሐምሌ ወር ፲፱፻፳፰ ዓ.ም አሌልቱ ላይ ፹፰ የጠላት የጦር ከባድ መኪናዎች(ካሚዮን) በተቃጠሉ ጊዜ የጦር መሪ የነበሩት አርበኞች ደጃዝማች ኃብተ ሥላሴ በላይነህና ፊታውራሪ ጂማ ሰንበቴ ነበሩ። ደጃዝማች ኃብተ ሥላሴ በዚሁ ጦርነት ላይ ሁለት የጠላት ከፍተኛ መኮንኖች ግድለዋል።

፪.ክቡር ደጃዝማች ኃብተ ሥላሴ በላይነህ በአሌልቱ ሜዳ ላይ ከኀዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ.ም ጀምሮ ሦስት ቀን ሙሉ የፈጀውን ጦርነት ባደረጉ ጊዜ ከጠላት በኩል የኢጣሊያ ፋሽስቶች ብቻ ፺፮ መኮንኖችና ወታደሮች ተገድለዋል።

፫.በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም ሸንኮራ አራራቲ ላይ በተደረገው ኃይለኛ ጦርነት ጄኔራል አውጎስቲኒን ገድለዋል።

፬.በ፲፱፻፴ ዓ.ም ቡልጋ ውስጥ ጨመሪ በተባለ ቦታ በተደረገው ከባድ ጦርነት ክቡር ራስ ደስታ ዳምጠውን እና እነደጃዝማች አበራ ካሳን የገደለውን ከፍተኛ የጠላት የጦር መሪ ገድለዋል።

፭.በግንቦት ወር ፲፱፻፴ ዓ.ም በቡልጋ የጉንጭ በተባለ ሥፍራ በተደረገው ብርቱ ጦርነት ጄኔራል ጋሊያኒን ገድለዋል።

ጀኔራል ጋሊያኒ በተገደለ ማግስት ስቻት በተባለው ሥፍራ የጠላት አውሮፕላኖች ብዙ ስንቅና ጥይት ለደጃዝማች ጦር ጥለዋል። ይህም ሊደረግ የቻለው ከጄኔራል ጋሊያኒ ላይ ብዙ የጦር መሣሪያና የአውሮፕላን ምልክት የሆነውን ሰንደቅ ዓላማ ስለማረኩ ነው። ከነዚህም ከገደሏቸው የጠላት መኮንኖች ላይ ብዙ ኒሻን ማርከው አሁን በቤተ መጻሕፍት መወዘክር ለመታሰቢያ ሰጥተዋቸው ይገኛሉ።

ነሐሴ ፲፱ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ/ም በጣልያኑ ኮሎኔል አድርያኖ ቶሬሊ የሚመራው ሠራዊት ቁልቋል በር ላይ ለመሸገው ሠራዊት በአምሳ ስምንት የጭነት መኪና ስንቅ አቀብሎ ወደ ጎንደር ሲመለስ አርበኞችና እንግሊዞች በጣሉበት አደጋ ላይ ከወገን ሠራዊት ፲፬ ሰዎች ሲሞቱ ከቆሰሉት ፴፱ ሰዎች መሃል እግራቸውን በጥይት የቆሰሉት አንዱ ደጃዝማች ኃብተ ሥላሴ ነበሩ።

ለጦር ሜዳ አገልግሎታቸውም ፦

የቅዱስ ጊዮርጊስ የጀብዱ ሜዳይ፤

የአርበኝንት ሜዳይ ፤

የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ሜዳይ፤

የኢትዮጵያ የድል ኮከብ ሜዳይ ፤

ከእንግሊዝ መንግሥት፦ የአፍሪካ ኮከብ እና የአፍሪካ የድል ኮከብ ሜዳዮች ተሸልመዋል ።

ከዚህም በኋላ የክቡር ዘበኛ ከፍተኛ መኮንን ሆነው በየቦታው እየተዘዋወሩ ፀጥታ ነሽዎችን አስከብረዋል በየአውራጃውም እየተመደቡ አስተዳዳሪ ሆነው ሰርተዋል በመጨረሻም ለህግ መወሰኛ ምክር ቤት አባልነት ተሹመው እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ አገራቸውን አገልግለዋል።



ክቡር ደጃዝማች ኃብተ ሥላሴ በላይነህ የክቡር ዘበኛ ከፍተኛ መኮንን

ክቡር ደጃዝማች ኃብተ ሥላሴ በላይነህ ፈጣሪያቸውን ፈሪ፤ ሀገራቸውንና ንጉሠ ነገሥታቸውን አፍቃሪ ፤ ድኅ መጋቢና አሳዳሪ ፤ ሽማግሌዎችን ጧሪ ፤ ጓደኞቻቸውን አክባሪ ነበሩ። ብዙ ጊዜ ያማቸው በነበረው የጉበትና የልብ ድካም ህመም ሚያዝያ ፲፩ ቀን ፲፱፻፷ ዓ.ም በተወለዱ በ፷ ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ግርማዊ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ፤ የተከበሩ ልዑላውያን ቤተሰቦች፤ የተከበሩ ሚንስትሮችና ከፍተኛ የጦር ባለስልጣኖች በተገኙበት በከፍተኛ ወታደራዊ ሥነ ሥርዓት በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ለሀገራችው ታላላቅ አገልግሎት ለፈጸሙ ጀግኖች አርበኞች በተዘጋጀው ሥፍራ በክብር አርፈዋል።

## ምንጭ


- ባንዲራችን ጋዜጣ ፩ ኛ አመት ቁጥር ፵፱ የካቲት ፲፰ ፲፱፻፴፬ ዓ.ም
- አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሚያዝያ ፲፪ ቀን ፲፱፻፰ ዓ.ም
- ጎንደሬ በጋሻው መፅሓፍ ከገሪማ ታፈረ ጥቅምት ፳፪ ቀን ፲፱፵፱ ዓ.ም
- ቼ በለው መፅሓፍ ከብላቴን ጌታ ማሕተመ ሥላሴ ወ/መስቀል ፲፱፻፰፩ ዓ.ም
- (እንግሊዝኛ) Barton, J.E.B. "The Campaign against Italian East-Africa (November 1941), The National Archives
- (እንግሊዝኛ) Shireff, David (1995, reprint 2009). *Bare Feet and Bandoliers: Wingate, Sandford, the Patriots and the Liberation of Ethiopia*. Pen & Sword Military. pp. 336 pages
- (ጣሊያንኛ) Battaglia di Gondar Vita e morte del soldato italiano nella guerra senza fortuna, Ed. Ferni - Ginevra 1973, libro I, pag. 183 e successive


ኢትዮጵያ በጀግኖች አርበኞቿ ከፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ ነፃ ለወጣችበት ለ፸ኛ ዓመት ክብረ በዓል ማስታወሻ ተዘጋጀ።

ኃብተሥላሴ ስለሺ(ጌቱ) ፓሪስ ፈረንሳይ